# “የጌታዬ፡እናት፡ወደ፡እኔ፡ትመጣ፡ዘንድ፡እንዴት፡ይሆንልኛል?”
## ሉቃስ፡ምዕ፡1፤43-44

በሐዘን፡ተውጬ፡ተቀምጬ፡ሳለሁ፤
የማደርገው፡ጠፍቶኝ፡ጣራ፡ጣራ፡እያየሁ፤
ስትመጪ፡ደስ፡አለኝ፡ብርታትን፡አገኘሁ፤
ድንግል፡እመቤቴ፡ሰላም፡እልሻለሁ።
በደዌ፡ተይዤ፡አልጋ፡ላይ፡ስውል፤
ፈውሱ፡ጭራሽ፡ርቆኝ፡እንደው፡ስዋልል፤
ዘመድ፡ሁሉ፡ከድቶኝ፡ለሞቴ፡ሲምል፤
ስትመጪ፡ደስ፡አለኝ፡ርህሩኋ፡ድንግል
እመቤቴ፡ማርያም፡ሆንሽኝ፡ለኔ፡ኃይል።
ዓለምን፡ወድጄ፡ከሷ፡ጋር፡ስውል፤
በሐጢአት፡ወድቄ፡ህጉንም፡ስሽር፤
ነፍሴን፡እየቀጣሁ፡ለስጋዬ፡ሳድር፤
ስትመጪ፡ደስ፡አለኝ፡የአምላክ፡ማህደር፤
ባንቺ፡ነው፡የምወጣው፡ከመከራ፡ጣር።
ማመስገኑን፡ትቼ፡ሐሜት፡ስናገር፤
መከራ፡እየቀጠልኩ፡በተንኮል፡ስንር፤
እውነትን፡ለውጬ፡በሐሰት፡ስቀይር፤
በበደል፡ላይ፡በደል፡ጨምሬ፡ስኖር፤
ስትመጪ፡ደስ፡አለኝ፡የሰው፡ልጆች፡ክብር፤
መግቢያውን፡አሳዪኝ፡የንስሀውን፡በር።
ስምሽን፡መጥራቱ፡ዳገት፡ሆኖብኝ፤
ብፅዕት፡መሆንሽን፡መስበክ፡አቅቶኝ፤
አማላጅ፡ነሽ፡ማለት፡ከቶ፡ተስኖኝ፤
እራሴን፡አፅድቄ፡ትዕቢቱ፡ይዞኝ፤
ስትመጪ፡ደስ፡አለኝ፡የሰው፡ልጅ፡እማኝ፤
ድንግል፡እመቤቴ፡ትህትናን፡ስጪኝ።
የነፍሴ፡ጠበቃ፡አለኝታዋ፡እናቴ፤
የኑሮዬ፡ትርጉም፡የሆንሽው፡ልማቴ፤
ስትመጪ፡ደስ፡አለኝ፡ቅድስት፡መድኃኒቴ፤
ምንኛ፡ጉዳት፡ነው፡ለኔ፡አንችን፡ማጣቴ፤
በድቅደቅ፡ጨለማ፡ሰውነቴ፡ተወሮ፤
ባዶ፡ሲሆንብኝ፡የዘይቴ፡ማሰሮ፤
ስትመጪ፡ደስ፡አለኝ፡አክብረሽ፡ቀጠሮ፤
ፈጥነሽ፡ልትሰሚኝ፡የልቤን፡እሮሮ።
ሰው፡በሰው፡ጨክኖ፡ለእስራት፡ተግዤ፤
ስትመጪ፡ደስ፡አለኝ፡ድንግል፡የኔ፡አጋዤ፤
ነፃ፡አውጥተሽኛል፡አልቀረሁም፡ተይዤ።
ወይን፡ጠጁ፡አልቆብኝ፡ሰው፡ሁሉ፡ሲቆጣ፤
መፍትሄው፡ጠፍቶብኝ፡የማደርገው፡ሳጣ፤
ስትመጪ፡ደስ፡አለኝ፡ድንግል፡የኔ፡ዕጣ፤
ያ፡የምልጃው፡ቃልሽ፡ከአፍሽ፡ሲወጣ፤
ውኃው፡ተለውጦ፡ወይን፡ሆኖ፡ተጠጣ።

ከኃይለመስቀል፡ተስፋዬ
ለንደን